ሰኔ 9ቀን 2009ዓ.ም (17.06.2017)

# <u>ለመሆኑ ሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ ማነው?</u>

*ዛሬ ሥለሻለቃ ዳዊት ማንነት መፃፍ ያሥገደደኝ ዋናው ምክንያት መንግሥቱ ኃይለማርያምን "ከዳሁ" ካለበት ጊዜ ጀምሮ ወያኔ አዲስ አበባ እሥገባበት ዕለት ድረስ ማለትም በውጭ አገር የስለላ መረብ ውስጥ ከመዘፈቅ ጀምሮ፣ ከሻዕቢያ፣ወያኔና አነግ ጋር ከነበረው ጥብቅ ግንኙነት እና በዚያም ሳቢያ በመፈንቅለ መንግሥቱ ምክንያት ጭምር የአገር መከላከያ መውደምን አሥመልክቶ የእሱ አሥተዋፃዖ እንደነበረበት ግልፅ ሆኖ ሳለ፣በሠራው ወንጀል አፍሮና አርፎ ከመቀመጥ ይልቅ፣ ለዳግመኛ ጥፋት ላይ ታች ሲል በመታዘቤ "ሕዝብ የማወቅ መብት አለው" ብዬ ሥለማምን፣ማንነቱን ማሳወቅ የግድ ሥለሆነ ነው።*

**ከምንጫችን ካገኘነው <u>ዕውነተኛ ታሪክ</u> ተነሥተን ሥለሻለቃው የምንለው ይኖረናል ተከታተሉን።**

*የመለዮ ለባሹ ንቅናቄ ከተጀመረ ቆየት ያለ ቢሆንም ዓላማና ደንብ አዘጋጅቶ መንቀሳቀስ የጀመረው ግን በ1971ዓ.ም በጥር ወር በአሜሪካን አገር ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ በመሰረተው የመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ነበር።"*

*የመንግሥቱ ኃይለማርያም ወዳጅና የቅርብ ሰው የነበረው ሻለቃ ዳዊት ለሥራ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ወደዋሽንግተን ካቀና በኋላ ከሕዝብ የሚያገናኘው ሰው ፈልጎ ኮሎኔል መንግሥቱን ለመታገል ቆርጦ እንደተነሳ ገለፀ።በዚህም መሠረት "<u>ከተት</u>" በተባለው ድርጅት ለመሳተፍ ሞከረ። ነገር ግን "<u>የከተት ህቡዕ ድርጅት</u>" አባል ከመቀበሉ በፊት ባህሪያቸውን፣የሕዝብ ደም ያለባቸውን፣የሕዝቡን አደራ የሸሹትን፣የሕዝብ ንብረት የዘረፉትን፣የሥልጣን ናፋቂዎችን ወዘተ ሠርገው እንዳይገቡ ለማጣራት ሲል፣ የሻለቃውን ሙከራ ውድቅ በማድረግ ሳይፈቅድለት ቀረ።።*

*አንድ የድርጅቱ አባል ግን ሻለቃው የወጣበትን ምክንያት "በማያሻማና በማያጠራጥር መልክ ለሕዝብ ሌተና ኮሎኔል መንግሥቱን በግልፅ በራዲዮና በፅሁፍ እንዲያወግዝ" ጠየቀ።ሻለቃው ሲነገረው መስማማቱ ቀፈፈው፣ሳይቀበለው ቀረ።*

*ድርጅቱ! ሻለቃው ይጠቅመኛል የሚለውን እርምጃ ሁሉ በመውሰድ ላይ መሆኑን አሥቀድሞ ደርሶበታል።ከዚህም በላይ <u>ከአሜሪካው የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት እየተመላለሰ የሚያሥፈልገውን ሁሉ በማድረግ ላይ እንዳለ ድርጅቱ</u> አውቋል።*

*በተባበሩት መንግሥታት ቢሮ የኢትዮጵያ መንግሥት አምባሳደር ሆኖ ቢሾም መክዳቱን እንደሚያቆም ከአቶ ካሳ ከበደ ጋር ሥምምነት ለማድረግ የመሞከሩም መረጃ ይፋ ሆነ።*

*ሻለቃው ወደአዲስ አበባ የማይመለስበት ጉዳይ እሱ ቀደም ሲል እንደገለፀው መንግሥቱን ለመታገል ሳይሆን በሻለቃ ለገሰ አስፋው ምክንያትና ቤቱ በመበርበሩና ይህንኑ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም መስማቱን በካሳ ከበደ በኩል ሥለሰማ ነበር።*

*መንግሥቱ ኃይለ ማርያምም የዳዊትን ቤት በረበሩ በተባሉት ላይ እርምጃ ለመውሰድ መርማሪዎች ወደ ዳዊት ቤት ይልካል።መርማሪዎቹም ከዳዊት ቤት ያገኙት ከአንድ አሮጌ ሱሪና አሮጌ ሻንጣ በሥተቀር ሌላ ነገር አልተገኘም።በዚህን ጊዜ ሻለቃው ተዘጋጅቶ እንደወጣ ግልፅ ሆነ።*

*በተባበሩት መንግሥታት የኢትዮጵያ ቢሮ ፀሐፊ የነበረችው አበበች መኮነን የተባለች ሻለቃው የተጠቀመበትን ቼክና አጉድሏል የተባለውን ገንዘብ የሚገልፅ መረጃ ነው የተባለውን ሁሉ አሰባስባ ወደአዲስ አበባ በአቶ ካሳ ከበደ አማካኝነት ላከች።*

*ከዚህ በኋላ "ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰበሰበ ገንዘብ ይዞ ከድቷል" በሚል ፀሐፊዋ ያቀረበችውን ቼክ በጋዜጣ በማውጣት ሻለቃው በራዲዮና በቴሌቪዥን ለሕዝብ እንዲጋለጥ ተደረገ።*

ሥለዚህ ከመንግሥቱ ጋር ሰላም ለመፍጠር ሲያደርግ የነበረው ሙከራ ሳይሳካ መቅረቱን ሲያረጋግጥ ድርጅት ወደአለበት ገብቶ በመታገልና ለመበቀል ከፍተኛ ጥረት ማድረጉን ቀጠለበት።የሚቀላቀለው ድርጅት ዕምነት እንዲጥልበት ሁኔታውን ማመቻቸት ሥለሚኖርበት መንግሥቱ የሰራቸውን ወንጀሎች ለማጋለጥ ሲደክም ታይቷል። በሌላ በኩል ደግሞ በመፈንቅለ መንግሥቱ ድርጅት ውስጥ ገብቶ ለመታገልና እርዳታም ለማስገኘት እንደሚችል ለግለሰቦች ቃል መግባቱ ይሰማል።

ዳዊትን “ከተት” ባይቀበለውም እና በኢሠፓ ውስጥ በነበረበት ጊዜ የፈፀማቸው በዝርዝር ባይታወቅም እሥኪጣራ ድረስ በህቡዕ በሚንቀሳቀሰው የመለዮ ለባሹ “የኢትዮጵያ ወታደሮች ንቅናቄ” ድርጅት እንዲገባ አመራሩ ቢቀበለውም አባላቱ ተቃውሞ ነበር። ነገር ግን ኮሚቴው ጠንካራና ደካማ ጎኖችን አቅርቦ በማሳመኑ አባል ሊሆን ቻለ።

ድርጅቱ ውስጥ እንዲቀላቀል ሲደረግ ከምክንያቶቹ አንዳንዶቹ፣ የደርግ ባለሥልጣን የነበረ ሠው ሲከዳ የሚያሥገኘውን ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባትና ድርጅቱ ከነበረበት ኢኮኖሚያዊ ውጥረት አንፃር ሻለቃው “ከአሜሪካ መንግሥት ድጋፍ አስገኛለሁ”በማለቱ የተመሠረቱ በመሆናቸው፣ በሻለቃው ማንነት ላይ ተነስተው የነበሩ ጥርጣሬዎችና ተቃውሞዎች እንዳይተኮርባቸው ሁኔታው አሥገድዷል። የሻለቃ ዳዊት ወደ ወታደሮች ንቅናቄ የመግባት የትግል ታሪክ ይህን ይመስላል።

ከዚያም በኋላ ዋሽንግተን በተደረገው ስብሰባ ለመጀመሪያ ጊዜ አብሮ ተሰበሰበ።ለቀጣዩ ሥብሰባ በስደት ላይ ያሉ ጥሩ ሥነ ምግባር ያላቸውን ሠዎች፣ አባላቱ ይዘው እንዲቀርቡ በተስማሙት መሰረት ዳዊት ብዛት ያላቸውን መኮንኖች ሥም ይዞ ቢቀርብም ከሻለቃ ስለሽ ፍሥሐና ሻምበል ፀጋየ በስተቀር ብዙዎቹ ከደርግ ጋር በሰሩበት ጊዜ ፀረ-ሕዝብና ንብረት የዘረፉ ሥለነበሩ ተቀባይነት ሳያገኙ ቀሩ። እነኚህ ሁለት መኮንኖች በአባልነት ተመዝግበው ከኮሚቴው ጋር እንዲሠሩ ሆነ።የእነዚህ ሁለት መኮንኖችና የሻለቃ ዳዊት ከኢትዮጵያ ወታደሮች ንቅናቄ ጋር የተቀላቀሉበት ዕውነተኛ ታሪክ ይህ ነው።

ነገር ግን እነኚህ ሦሥት መኮንኖች “የኢትዮጵያን ወታደሮች ንቅናቄ ቦስቶን ላይ የመሠረቱት እነሱ እንደሆኑ አድርገው የሀሰት ታሪክ ፈጠሩ።ሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ ቀድሞ የተፈጠረውንና ደጅ ፀንቶ የገባበትን “የኢትዮጵያ ወታደሮች ንቅናቄ” እሱ እንደፈጠረው አድርጎ ያቀረበው የታሪክ ሽሚያ ፍፁም ሀሰት ነበር።ለመግለፅ የተሞከረው በብዙ ሰዎች ዘንድ የሻለቃ ዳዊት ሚና አወዛጋቢ ሆኖ ያለማቋረጥ የቀጠለ ስለሆነ ትክክለኛ መልኩን ለማስጨበጥ ነው።

ይህ ንቅናቄ እየሰፋ ከመጣ በኋላ የድርጅቱ መጠሪያ “የኢትዮጵያ **ነፃ** ወታደሮች ንቅናቄ”ተብሎ ተሰይሞ በህቡዕ ሥራውን ጀመረ።

የንቅናቄውም ዓይነተኛ ትኩረት መፈንቅለ መንግሥት ማድረግ ነው።በደርግ ላይ እጃቸውን ያነሱም ይሁን በአንደበታቸው የተቃወሙ የተቃዋሚ ድርጅቶች ሁሉ ጋር ልዩነት ሳይደረግ ግንኙነት መመሥረት እና የጋራ ለሆነው አገራዊ ጉዳይ መሥራት እንዳለበት ይገልፃል።ሥለዚህ ኢሕአፓን፣ መኢሶን፣እነሻዕቢያንና ወያኔን ጨምሮ ግንኙነት ለማድረግ ወጠነ።

**የመጀመሪያ ልዑክ ወደሱዳን-ኤርትራ ላከ ።** መፈንቅለ መንግሥት ሲደረግ ሻዕቢያና ወያኔ አጋጣሚውን ተጠቅመው በሠራዊቱ ላይ አደጋ እንዳይጥሉ የጋራ ኮሚቴ አቋቁሞ አሥተማማኝ ዋስትና የሚገኝበትን ተግባራዊ ለማድረግ ሱዳንም ኤርትራም ድረስ ልዑክ በመላክ፣አሜሪካን አገርም ተገናኝቶ በመነጋገር የመጀመሪያ ሚሽኑን ተወጣ።

ይህ በዚህ እንዳለ፣ለመጀመሪያ ጊዜ ሻለቃ ዳዊት በሥለላ ወጥመድ ውስጥ ከወደቀው ኢፒዲኤ ተወካይ (የእነደረጀ ዴረሴን በስለላ መዋቅር ውስጥ የተካተተው ከበሥተጀርባ በሦሥት አሜሪካውያን ሠላዮች የሚመራው)ጋር እንደተነጋገረና ሀሳቡ እንደጣመው አባል ከሆነበት ድርጅት ከነፃ ወታደር ንቅናቄ ጋር ተወያይቶ፣ድርጅቱ ሀሳቡን ውድቅ እንዳደረገውና እንዳልተደሰተበት ይታወቃል።

የዚህ ዶሴ ከተዘጋ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሻለቃው! የገንዘብ ርዳትን በተመለከተ ብዙ ደከምኩበት የሚለውን፣ ድርጅቱ ራሱ ከአሜሪካውያን አንደበት ለመስማት በግንቦት ወር **1989ዓ.ም** ከኢትዮጵያና ከሱዳን የመጡትን ጨምሮ፣ 9 ሰዎች ያሉበት ቡድን ይዞ ወደስብሰባው ቦታ አመራ።ወደሆቴሉ ግቢ ሲገባ በድብቅ ቪዲዮ ካሜራዎች ከመደቀናቸውም ባሻገር ሁኔታው የሚያጠራጥር የተለያዩ ነጮች ተራ በተራ ወጣ ገባ የሚሉበት ከመሆንም ያለፈ በመሆኑ፣ በስብሰባው ላይ ለመገኘት የሄዱት መኮንኖች በተደራጀ የትኩረት ወጥመድ ውስጥ እንገባለን የሚል ቅንጣት ጥርጣሬና ግምት አልነበራቸውም።

ከዚያ ዳዊት ወደ 3ኛ ፎቅ ወስዶ የአሜሪካዊ ጓደኛው ወደሌላ ቦታ ሥለሄደ "ቤቱን አውሶኝ ነው" በሚል ጠባብ ክፍል ውስጥ አስገባቸው።ዳዊት ዘግይቶ ሥለመጣ፣የዘገየውም ከአሜሪካውያኑ ጋር ሲወያይ እንደነበር ገልፆ በአማካሪው በኩል "የኢፒዲኤን አቋም እንደገና መመርመር አለባችሁ" እንደተባለም አሥረዳ።መኮንኖቹ ተንኮል መሸረቡን እና በአካባቢያቸው ድምፅ የሚቀርፁ መሣሪያዎችም እንደተደቀኑ ሥለተረዱ አንዳቸውም ትንፍሽ ሳይሉ "ሥለመሸብን ወደየቤታችን" በማለት ሥብሰባውን በትነው ተመለሱ።

በማግሥቱ ዳዊት ለአንዱ ጓደኛው መኮነን በስልክ "አሜሪካኑ ሊያነጋግሩን ነውና ፈጥነህ ድረስ"ብሎ ሲጠራው፣የሀገር ጉዳይ ነውና ከ30 ማይል ርቅት መኪና ነድቶ ይሄዳል።ዳዊትም ወዲያው ከአሜሪካዊያኑ ጋር ተነጋግሮ እንደተደሰተበት ለመኮንኑ ይነግረዋል።ዳዊት ይህን ያደረገው የድርጅቱ አባላት በንዴት እርምጃ እንዳይወስዱበት ያደረገው ማደነጋገሪያ ነበር። በጣም የሚገርመው ሻለቃው ያሳዬው አቀራረብ፣ የአራዳ ልጅ የሚያደርገው ዓይነት ነበር።

**ሁለተኛ ልዑክ ወደሱዳን-ኤርትራ ሄደ።** የሁለተኛው ቡድን ወደኤርትራ፣ትግራይ፣ካርቱምና አመቺ ናቸው በሚላቸው ሥፍራዎች ተዘዋውሮ ለትግል የሚሆኑ ቦታዎችን ለመምረጥና ከድርጅቶችም ጋር ለመነጋገር ወደካርቱም እንዲመጣ እና ካርቱም ከሚገኘው የነፃ ወታደሮች ንቅናቄ ኮሚቴ ጋር ግንኙነት በማድረግ በሚነገረው መሥመር እንዲንቀሳቀስ ልዩ መልዕክት በልዩ ኮድ ከካርቱም ወደአሜሪካ ተላለፈለት።

በዚህ ጊዜ በንቅናቄው ሠዎች መካከል ችግር ተፈጥሮ ሥለነበር ለተነሳው አለመግባባት እልባት ሳይበጅለትና መሄድ የሚገባቸው መኮንኖች ሳይካተቱ፣ ሻለቃ ዳዊት የራሱን ጓዶች ሻለቃ ስለሽ ፍስሀና ሻምበል ፀጋዬ ያሉበት ቡድን ፈጥሮ በራሱ ውሳኔ ከኒውዮርክ ተነስተው ካርቱም ገብተው ለኤርትራው ሕዝባዊ ግንባር (ለሻዕቢያ) እጃቸውን ሠጥተው ባዘጋጀላቸው መጠለያ ገቡ።

ለሻዕቢያዎች የዳዊት በወዶ ገባነት በእጃቸው መውደቅ ትልቅ ነገር ነበር፣ምክንያቱም በኤርትራ አገረ ገዥ ሆኖ ከመሥራቱም በላይ የቀይ ኮከብ ዘመቻ ደጋፊና አዘጋጅም ሥለነበረ።በመሆኑም ዳዊት በእጃቸው ከገባ በኋላ እንዳይለቀቅ የሻዕቢያ ሠራዊትና ደጋፊዎቻቸው ቢያንገራግሩም፣ የኮሎኔል መንግሥቱ የቅርብ ወዳጅ ሆኖ በአሥተዳደሩ ውስጥ ትልቅ ሚና ሥለተጫወተ የሚያውቀውን ምሥጢር፣እንቅስቃሴና ቁልፍ የሆኑ ወታደራዊ አዛዦች ሁኔታ ከፖለቲካ ጥቅሙ አንፃር የመጀመሪያ መረጃ ለማግኘት ሲባል የተመኙትን መጥፎ እርምጃ ከመውሰድ ተቆጥበዋል።

የዳዊት ቡድን ከአሜሪካ በተነሳ በ3ኛው ቀን ወደኤርትራ ተጉዞ "ሻክብ"ከተባለው ከዋናው የሻዕቢያ የአመራር ጠቅላይ ሠፈር ደረሰ።

ከዚያም ወደዋሻቸው ወስደው ካስጎበኟቸው በኋላ፣ "በዳዊት ላይ እርምጃ እንውስድ አንውሰድ" የሚል ጭቅጭቅ እንደገና በሻዕቢያዎች መካከል ተነሥቶ፣ የፖለቲካ ጥቅሙ እጅግ ሥለሚጠቅማቸው፣ ሊወስዱ ካሰቡት አሥከፊ እርምጃ ተቆጥበው 5 ሻዕቢያዎች እነዳዊት ወደአረፉበት ቤት ማታ ወንድማዊ ውይይት ሲያካሂዱ ቆዩ።በዚህ ጊዜ ዳዊት በደስታ ተውጦ የሞቀ ውይይት ሲያደርግ አመሸ።

ለሁለተኛው ጊዜ ከሻዕቢያ ጋር ሥብሰባ ሲደረግ እነሻለቃ ዳዊት ከአዲስ አበባ "ከእነጄኔራል መርዕድ ንጉሴና ጄኔራል ፋንታ በላይ የተላከ መልዕክት ነው"ሲሉ የሚከተለውን ሀሳብ አቀረቡ።ሀሳቡም

“በቅርቡ የኢትዮጵያ ሠራዊት መፈንቅለ መንግሥት በማድረግ መንግሥት ለመለወጥ ዕቅድ ሥላለው፣ ይህ ሲከናወን ሕዝባዊ ግንባር(ሻዕቢያ) በሠራዊቱ ላይ እርምጃ እንዳይወስድ ቃል እንደትገቡና በራዲዮና በፅሁፍ ከ15ቀናት በፊት በመግለጫ አሳውቁ”የሚል ነበር።

ሻዕቢዎችም ካደመጡ በኋላ “ከ15ቀን በፊት ጉዳዩ ከታወቀ የሚገለበጠው ይነቃ የለሞይ? እርምጃችሁ እንደተቃረበ ንገሩን፣በእኛ በኩል ማንኛውንም ለማድረግ ቃል እንገባለን” ማለታቸው ሲታወቅ በጀኔራሎቹ የሚወሰደው እርምጃ ግን ከፍተኛ ሥጋት ላይ ጥሏቸው ነበር ።

ዳዊትም ከምርኮኞቹ ብዙ ሥድብ ቢደርስበትም፣ከኤርትራ ወደሱዳን ጉዞውን ቀጠለ።ከሱዳንም ወደአሜሪካ አቀና። አሜሪካም እንደገባ ያከናወነውን፣ለመፈንቅለ መንግሥቱ ኃላፊዎች ለሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይና ለሜጀር ጄኔራል መርዕድ ንጉሴ ሪፖርት አደረገ።

ሻለቃ ዳዊት አሜሪካን አገር ከገባ ጀምሮ በጥቂት ወራት ውስጥ በኑሮውም በኩል የተደላደለ በመሆኑ የመፈንቅለ መንግሥት ንቅናቄው አሠራርም የመፃፃፍ፣የመላላክ፣የሥልክ፣የፋክስና የኮምፒውተር እንዲሁም ፖስታ ግንኙነት ሁሉ በእሱ በኩል እንዲሆን የግድ ነበር።

አዲስ አበባ ከሚገኙት አዛዦች የሚደርሰውን ዕቅድና ትዕዛዝ እየተቀበለ ለሚመለከታቸው ክፍሎች የሚያሥተላልፈው በውጭ የሚገኘው ወታደራዊ ክፍል ተጠሪ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ ነበር።

ሻለቃ ዳዊትና ኮሎኔል መንግሥቱ የቅርብ ወዳጆች ናቸው።የሕዝብ ደህንነት ኃላፊው ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴ እና የኮሎኔል መንግስቱ ልዩ ፀሀፊና ረዳት መንግሥቱ ገመቹ ደግሞ የጠበቀ ግንኙነት አላቸው።

እነዚህ ሁለቱ ቁልፍ ሠዎች የሻለቃ ዳዊት ጓደኞች ናቸው።የዳዊትን ጓደኝነት መገደብ ሥለማይቻልና ግንኙነቱ ለእንቅስቃሴው ሊረዳ ይችላል የሚል ግምት ሥለነበር ተወደደም ተጠላም ባልንጀርነታቸውን እንዲቀጥሉበት ተደርጓል።

እነዚህ ሁለቱ ጓደኞቹ ፣በራሱ በሻለቃ ዳዊት አማካይነት ተይዘዋል ይባል እንጅ፣ ከነሱ የተሰጡ ተብለው በሻለቃ ዳዊት የሚቀርቡ መረጃዎች ገና ከጅምሩ በጣም የሚያጠራጥሩ እንደነበሩ አይዘነጋም።

ባንፃሩ ግን በኢትዮጵያ ነፃ ወታደሮች ንቅናቄ በኩል የሚካሄደውን እንቅስቃሴና ሴራ በሻለቃ ዳዊት አማካይነት እነርሱ በሚገባ ያገኙ ነበር።

ሻለቃ ዳዊት አዲስ አበባ ከሚገኙት ጄኔራሎች ጋር እየተገናኘ ሁኔታውን የማመላከት ኃላፊነት እንደነበረው ግልፅ ነው።ባንፃሩም ከሕዝብ ደህንነቱ ከኮሎኔል ተስፋዬ ወልደ ስላሴና ከፕሬዝደንቱ ረዳት ከመንግሥቱ ገመቹ ጋር የዕለት በዕለት ግንኙነት ነበረው።

ግንቦት 8ቀን 1981ዓ.ም በእነኮሎኔል ተስፋዬ ወልደ ስላሴ አቀነባባሪነት ኮሎኔል መንግሥቱ ከታቀደው መፈንቅለ መንግሥት አደጋ እንዲያመልጥ፣የሀሰት ጉብኝት በማመቻቸት ከቤተሰቡና ከቅርብ የሥራ ባልደረቦቹ ጋር ወደምሥራቅ ጀርመን በድንገት ሾልኮ እንዲሄድ ተደረገ።

ይህን ምስጢራዊ ነበር ተብሎ የተገመተውንና የታመነበትን ግን የከሸፈውን የመፈንቅለ መንግሥት ሴራ ከመሩት ጄኔራሎች ጭምር በጥቂቱ ከዘጠና ስድስት(96) በላይ የሚሆኑ ከሜጀር ጄኔራል እሥከ መቶ አለቃ ማዕረግ የነበራቸው ውድና ብርቅዬ የአገር ሀብቶች፣ ተወንጅለው ተገድለዋል፣ታሥረዋል።

**ይህን ያህል የመከላከያ ኃይል ማጣት አገርን ማራቆት በመሆኑ፣ ለመንግሥቱ ኃይለማርያም የመውደቅና ለወንበዴዎች የሥልጣን ጉዞ ጥርጊያ መንገድ እንደከፈተ አይጠረጠርም።**

በሻለቃ ዳዊት ሪፖርት ብቻ የተጠቀሱት ሠዎች ያለጥርጥር በመፈንቅለ መንግሥቱ ዕቅድ እንደሚስማሙበት እየተደረገ ዘወትር ይቀርብና ይሰማ በነበረው <u>የሻለቃ ዳዊት መረጃ ዕምነት ተጥሎ</u> ነበር።

እንደዚህ ያለው ግንኙነትና አሠራር የመፈንቅለ መንግሥቱን ምሥጢር በቅድሚያ እንዲታወቅ በማድረጉ በእነዚህ ሠዎች አማካይነት የእነጄኔራል መርዕድ ንጉሴ ዕቅድ አደጋ ላይ መውደቁ ትክክለኛ ነው ከተባለው መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል።

ክህደት ፈፃሚዎቹ ኮሎኔል ተስፋየ ወልደ ስላሴና መንግሥቱ ገመቹ ከሻለቃ ዳዊትና ከእነጄኔራል ፋንታ በላይ ጋር ግንኙነት ነበራቸው።የውጭውንና የውስጡን እንቅስቃሴ በጥብቅ እየተከታተሉ፣ በጥቁር መዝገብ እየመዘገቡ እሥከመጨረሻው ድረስ ለማወቅ እንደቻሉ ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደ ስላሴ በመጨረሻ ላይ በሰጠው ቃል ተረጋግጧል።

የነፃ ወታደሮች ንቅናቄ ለመፈንቅለ መንግሥት የሁለተኛ ዙር ዕቅድ በማውጣት ላይ እንዳለ ፣ሻለቃ ዳዊት ከመፈንቅለ መንግሥቱ መክሸፍ በኋላ፣ ቀደም ብሎ ሲሰራው በነበረው የረቀቀ ተንኮል ብቻ ሳይሆን በግልፅም ጭምር ችግሮች መፍጠሩን ቀጥሏል።

1.ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ ከደርግ ኢሥፓ መንግሥት ከድቶ የነፃ ወታደሮችን ንቅናቄ ከተቀላቀለበት ጊዜ ጀምሮ ሲፈፅማቸው የነበሩት አፍራሽ ተግባራት ኢሕአዴግ አዲስ አበባ እሥከገባበት ድረስ <u>በጥርጣሬ ይታይ</u> እንደነበር ቀደም ሲል ተወስቷል።

2. <u>ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሻዕቢያ በሻለቃው ላይ እርምጃ ያልወሰደው፣ሻለቃው" የሚያውቀውን **ምሥጢር፣እንቅስቃሴ** እና ቁልፍ የሆኑ **ወታደራዊ አዛዦች ሁኔታ** ከፖለቲካ ጥቅሙ አንፃር የመጀመሪያ **መረጃ** ለመግኘት" በመሆኑ</u>

(ሀ) እነኮሎኔል ተስፋዬ ወልደ ስላሴና መንግስቱ ገመቹ፣ ከጄኔራሎቹ ጋር እንደማይጓዙና መፈንቅለ መንግሥቱን በቅድሚያ እንደሚቀጩት እየታወቀ፣ በሚገባ ተደራጅተው በቁርጠንነት ርምጃዎችን ለመውሰድ የተነሱትን የመፈንቅለ መንግሥት ጄኔራል መሪዎችና አሥተባባሪዎች እያሥለቀመ ማሥመታት የተከሰተው፣ የነፃ ወታደሮች ንቅናቄን ድርጅት ከጊዜ በኋላ የተቀላቀለውንና በአመራሩ ውስጥ በመግባት የግል ውሳኔ በማድረግ ላይ የነበረውን <u>ዳዊት ወልደጊዮርጊስን</u> ነው።

(ለ) በምፅዋው ጦርነት ለአገሩ በጀግንነት የወደቀው ብርጋዴር ጄኔራል ተሾመ ተሰማ በባህር የመጣለትን መሣሪያ ሠዎች እንዳያወርዱ ብርጋዴር ጄኔራል አሊ ሀጅ አብዱላሂ የ3ኛው መካናይዝድ ክፍለ ጦር አዛዥ ከማሥከልከሉም በላይ ከብርጋዴር ጄኔራል ጥላሁን ክፍሌ የ606ኛው ኮር ዋና አዛዥ ጋር በማበር፣ ያላንዳች ውጊያ ጦሩ እንዲፈታ በማድረግ እጃቸውን እንዲሰጡ ተደርጓል።እነዚህ ሠዎች ላደረጉት አገር የመበተን ውለታ በክብር ቆይተው ወደአዲስ አበባ ሄደው ሥራ ይዘው እንደነበር ይታወቃል።ይህንንም ሻዕቢያ ከሻለቃው የፈለገው <u>**የወታደራዊ አዛዦች ሁኔታ መረጃ**</u> ከመሆን አይዘልም።

በነገራችን ላይ ተስፋዬ ኢህአዴግ ወደወህኒ ካወረደው በኋላ በነበረበት እሥር ቤት ሆኖ በ1985ዓ.ም "ሳሌም" ለሚባል መፅሔት ከሰጠው ቃለ መጠይቅ ላይ የሚከተለው አጭር ምሥክርነት ይገኛል። <u>"የኤርትራን ጉዳይ መድረክ በመፈለግ በቅድሚያ ከኢፒኤሌፍ(ሻዕቢያ) ከዚያም ቀጥሎ ከኢኤልኤፍ(ጀብሃ) ጋር ...ውይይቶችን አድርጌአለሁ.....የወታደራዊ እርምጃውና ፖለቲካው ጎን ለጎን ሄዶ ቢሆን ኖሮ....በኢትዮጵያዊነቴ የማዝነው እነዚህ ነገሮች ተግባራዊ ባለመሆናቸው ነው።**ኤርትራ እንድትገነጠል ምክንያት ከሆኑት ሰዎች መሃል አንዱ በመሆኔ ይቆጨኛል**</u>" በማለት ኃላፊነቱን ወስዷል።ሻለቃውስ ከእነሻዕቢያ ጋር ሆኖ ለሠራውና አሁንም ለሚሠራው ወንጀል ይናዘዝ ይሆን? ወይስ መፅሐፍ ፅፎ "ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ወዳጅነት አበርክቻለሁ" እያለ ማፌዙን ይቀጥልበታል?

3. የነፃ ወታደሮች ንቅናቄ ኮሚቴ ከህደት ፈፃሚዎቹ ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደ ስላሴና መንግሥቱ ገመቹ "መወገዝና መጋለጥ አለባቸው" የሚል ውሳኔ ሲያሳልፍ ሻለቃ ዳዊት አጥብቆ ተቃወመ።

4 ከመፈንቅለ መንግሥቱ መክሸፍ በኋላ፣የነፃ ወታደሮች ንቅናቄ! ይጠቀምበት የነበረው የመረጃ መሥመር፣ እና ከመሀል አገር፣ከሱዳንና ከአጎራባች አገሮች የነበሩት ግንኙነቶችም እንዲሁም ከኢትዮጵያ የሚላኩና በየቦታው የተቋቋሙትን ኮሚቴዎች ሁኔታ የሚገልፁ ደብዳቤዎች መቋረጣቸውን ሥንገነዘብ፣ይህን ረቂቅ ምሥጥር እየተከታተለ የሚያስመታና የሚያወድም ሻለቃው እንደነበር ግልፅ ነው።

5.ሻለቃ ዳዊት! የኢትዮጵያን መበታተን ሲመለከት ተልዕኮው ማብቃቱን በማረጋገጥ፣የድርጅቱን እንቅስቃሴ ለማቆም በአባላቱ መካከል ብጥብጥና አንጃ ፈጥሮ፣ንቅናቄውን አኮላሽቶና በታትኖ ከትግል አጋሮቹ መሰወሩ ለጥፋቱና ለጥቃቱ ሙሉ ሃላፊነትን ከመቀበል ሌላ ተጨማሪ ማሥረጃና ትንታኔ የሚያሻው አይሆንም።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አንጎላ በተባበሩት መንግሥታት በኩል ሥራ እንደያዘና ከእነሻዕቢያ ጋር የግል ግንኙነት ፈጥሮ ኬንያ ለመገናኘት ማቀዱ ታወቀ።ከሻዕቢያ፣ወያኔና አነግም ጋራ አገር እሥከሚቆጣጠሩ ድረስ ከጎናቸው ሆኖ ሠርቷል።

ይህ በዚህ እንዳለ ወያኔ(ኢሕአዴግ)አምቦ እሥከሚደርስ ድረስ ሻለቃ ዳዊት ጋር ግንኙነት ነበራቸው፣ ባለውለታውም ነበር። አምቦ ሲደርስ ግን ግንኙነቱ ቆመ።ሻለቃውም ተስፋ ሳይቆርጥ መጠባበቁን ቀጠለ።

ወያኔ አዲስ አበባ እንደገባ ሻለቃ ዳዊት ለፕሬዝዳንት መንግሥቱ የፃፋቸውን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ተደብቀው የነበሩትን የምሥጥር ደብዳቤዎች ይፋ በማድረግ <u>በጋዜጣ፣በራዲዮና በቴሌቪዥን</u> ላይ አወጣው። ሻለቃውም ወደኢትዮጵያ ለመግባት የነበረው ዕቅድ ሁሉ ውሀ እንደበላው ተረዳ፣እርሙንም አወጣ።

አንደኛው ደብዳቤ የተፃፈው የካቲት 1978ዓ.ም ሲሆን፣የተፃፈውም በእጅ ነው፣ከፊርማው ጋር "ሁልጊዜ ታዛዥ ወንድምዎ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ" የሚል አለበት። ከተፃፉት መካከል የሚከተሉት አሥገራሚና አሣፋሪ ዓረፍተ ነገሮች ይገኙበታል"<u>.....ለኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት አመራር ከእርስዎ ሌላ አማራጭ የለውም ብዬ ሥለማምን.....</u> " ካለ በኋላ <u>"ለእርስዎ ቅርብ የሆኑ ሀቅ የሚናገሩ ብዙዎች አይደሉም፣ በአሁኑ ወቅት በጣም ቅርብ ከሆኑት መካከል ጓድ ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን፣ጓድ ተስፋዬ ወልደስላሴ፣ጓድ መንግሥቱ ገመቹ በስተቀር፣አካባቢዎ ካሉ ሠዎች መካከል ሀቅ የሚናገር የለም።"</u> ከዚህም በላይ ብዙ ብሏል።

<u>ሻለቃው በሚሥጥር በዛ ያሉ ደብዳቤዎችን ፅፎ ለፕሬዝዳንት መንግሥቱ በኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴና በመንግሥቱ ገመቹ እጅ በድፍረት ላከ።የደብዳቢዎቹ ይዘት ደግሞ የሌሎች ባለሥልጣናትን ሥም በመዘርዘር "እከሌን ይመኑ፣እከሌን አይመኑ፣እከሌን አይውደዱት" እያለ የሚጠላቸውን ሠዎች ለማስመታት</u> ያደረገው ጥረት በዕውነት ያሳዝናል።

ዳዊት የኮሎኔል መንግሥቱን አስተዳደር ለመጣል እታገላለሁ በማለት ሥልጣኑን ትቶ በመክዳት እና "ቀይ እንባ" በተሰኘው መፅሐፉ መንግሥቱን አብጠልጥሎ ለመውቀስ የማይፈራ ደፋርና ቁርጠኛ የኢትዮጵያ የሕዝብ ልጅ እንደሆነ ለማሳዬት ሲጣጣር፣የሰማውና ያወቀው ወገን፣ አቋሙን አድንቆ ድጋፉን በመቸር በተቃዋሚው ጎራም አመራር ይዞ ታዋቂ እንዲሆን ረድቶታል።በዚህ ደረጃ ላይ ይገኝ የነበረው ሻለቃ <u>በግልና ምስጥራዊ በሆነ መንገድ ከኮሎኔል መንግሥቱ ጋር ግንኙነት መፍጠሩ፣</u> በሕዝብና በአገር ላይ የሚቀልድና የሚነግድ ለመሆኑ <u>በሰነድ በመረጋገጡ፣</u> <u>የሻለቃውን ምንነት</u> ፍንትው አድርጎ ሥላሳዬ በተቃዋሚዎች ዘንድ የተቸረውም ድጋፍ ጨርሶ ሊጠፋ ቻለ ።

ሻለቃው!“ኢትዮጵያ እያለሁ በመንግሥቱ ፊት ሳይቀር የልቤን ለመናገር ድፍረቱ ነበረኝ ወዘተ ወዘተ” ይል እንደነበረው በስደት እያለስ መንግሥቱን በምሥጥር ሲገናኝ እንደሚለማመጠው ነው ወይስ በእውነተኛ ማንነቱ ይገልፀው ይሆን? ለማንኛውም ዝርዝሩ በራሱ በዳዊት  የእጅ ፅሁፍ በየካቲት እ.ኢ.1978ዓም ከተፃፈው ደብዳቤው ይገኛል። ሁሉንም የደብዳቤውን ይዘት መፃፍ ሥለማይቻል ፈላጊው ብዙ ከሆነ ወደፊት ዘዴ ይፈለግለታል።

**መደምደሚያ!** እነኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴና  መንግሥቱ ገመቹ የዳዊት ጓደኞች እንደሆኑ ቢታወቅም ፣መፈንቅለ መንግሥቱን በሚመለከት ከጄኔራሎቹ ጋር ያገናኛቸው እና ለደረሰው ክሽፈትና የነፍስ መጥፋት በቅድሚያ ተጠያቂው ሁለት ሥለት ባለው ቢለዋ የሚበላው ዳዊት እንደሆነ መታወቅ አለበት። የመፈንቅለ መንግሥቱ ጄኔራሎች “ከመሃላችን ሠው ከዳን” ሲሉ ተደምጠዋል። ያ ከዳ የተባለው ሠው አንድ ብቻ ሳይሆን 3ናቸው ኮሎኔል ተስፋዬ፣መንግሥቱ ገመቹ፣ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ ናቸው።

--ለሻለቃው! በሻዕቢያ ላለመገደል ምክንያት የሆነው በቂ መረጃዎች በመሥጠትና ኢትዮጵያን በመበተን ታማኝነቱን በማብሰሩ እንደሆነም ይነገራል።

መፈንቅለ መንግሥቱ ቢሳካና ጄኔራሎቹ ቢተኩና የኢትዮጵያ ጦር እንደገና ቢጠናከር ሻዕቢያም ሆነ ወያኔ እንደገና ከተጠናከረ ኃይል ጋር መግጠም የበለጠ ሥለሚከብድ  እናም መፈንቅለ መንግሥቱ እንዳይሳካ ዳዊትን ይዘው አሁንም አሁንም ዜናዎችን ከመከታተልም በላይ ባሏቸው የውስጥ አርበኞችም ጥረት ከማድረግ አላቆሙም ነበር።ሳይሳካ ሲቀርና ሲከሽፍ ተገንጣዮቹ ተደሰቱ፣ ከምክንያቶቹም ዋናው በመክሸፉ ቁጥር ሥፍር የሌለው የመከላከያ ኃይል ማጣት አገርን ማራቆት በመሆኑ፣ ለመንግሥቱ ኃይለማርያም የመውደቅና ለወንበዴዎቹ የሥልጣን ጉዞ  መፋጠን ጥርጊያ መንገድ በመክፈቱ።  በኋላም  ሠራዊቱ በአሻጥር ለመበተን በቃ። እሥካሁን በዝርዝር የቀረቡትን ከተከታተልን ዳዊት!ቀደም ሲል ወደፖለቲካው ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ  የሠራቸው ሁሉ አፍራሽ እንጅ አንድም ገንቢ ነገር አለመኖሩን እንረዳለን።

እነኚህን መጠነ ሠፊ አሳፋሪ ታሪኮች  የሠራው ሻለቃ ዳዊት፣ የሠራውን ሥራ የሚያውቁበት ሠዎች “ሞተው አልቀዋል” ወይም ጊዜው ሥለረዘመ “ተረስቶልኛል” ብሎ ካላሰበ፣ወይም የዶሮ ዓይን ካልበላ በስተቀር፣ ማፈር ሥለሚኖርበት ዳግመኛ ወደፖለቲካው መስክ መጥቶ ለዳግመኛ ጥፋት  ይዘጋጃል ብሎ ማሰብ ይከብዳል።

ያም ሆነ ይህ  “የለመደ ልማድ ያሥርቃል ከማዕድ” እንደሚባለው ሻለቃው!ከወያኔ ቢለያይም ከሻዕቢያና ከኦነግ ጋር  እንዲሁም በወያኔ ምትክ ብርሀኑን ይዞ ዛሬም እንደትናንቱ፣አገሪቱንና ሕዝቧን በድጋሜ ለመቅበር  ብቅ ብሏል።

-የደርግ ኢሠፓ መንግሥትም የሻለቃውን ክህደት አሥመልክቶ ድርጊቱ ቤተሰባዊና የውርስ ባህርይ(የባንድነት ዘር አለው ማለት ነው) እንደሆነ ይፅፍበት የነበሩት መጣጥፎች  ለመበቀል የሚያስገድድ ዕውነታ እንደሚታይበት ምሥክርነቱን ገሀድ ያደርገዋል።

-ራሱን ከመካብ አልፎ፣ሥለአባቱም  ከማፈር ይልቅ በኩራት ሲያነሳ ተደምጧል። እንደሚታወቀው ኢጣሊያ ከወጣ በኋላ አፄ ኃይለስላሴ  ወደአገር እንደገቡ፣ ብዙ የኤርትራና የትግሬ ባንዳዎች፣ እንዲሁም ጥቂት የቀሪዎቹ  ዘሮች  ባንዳዎች ወደሹመት መምጣታቸው አይካድም።የሻለቃ ዳዊት አባትም አንዱ ናቸው።

የሻለቃ  ዳዊት ባንዳነትም ከዘር ተያይዞ ለመምጣቱ ዋናው ማሥረጃ  ከሰራቸውና ዛሬም ከሚሠራቸው ተግባሮቹ ባሻገር የአባቱ እንዲሁም የወንድሙ የሙሉጌታ ወልደጊዮርጊስ  ልክ እንደወንድሙ ከሀዲ መሆን ነው።

ዳዊትን፣ወያኔ አንቅሮ ሥለተፋው ነው እንጅ ቢቀበለው ኖሮ ገስግሶ የሚሄድ ሞራለቢስ ባንዳ እንደሆነ ይሰመርበት።

-ለነጭ የሥለላ መረብ የተንበረከከው ዳዊት! የውጭ አገር የሰላይ ድርጅት እየጎተተ የአገር ህልውናን በቀላሉ በማጥፋት የተካነ በመሆኑ፣ በራስ ላይ መተማመንን መሠረት በማድረግ አባቶችቻችን ከነጭ ተፅዕኖ ነፃ አድርገው ያቆዩትን የራስን ማንነትና የአገርን ምንነት ለባዕድ አሳልፎ የሰጠ ወኔ የከዳው ተንበርካኪ እንደሆነ ይታወቃል።

ዛሬም እነሊንጮና እነብርሀኑ (በሻዕቢያ ጠልቃ ገብነት ይመስላል) ዳዊትን ጎትተው ያመጡት ለዚሁ ተግባሩ በተካነው መንገድ በጌቶቻቸው አማላጅነት ከወያኔ ጋር ሥልጣን ለመቀራመት ለሚያደርጉት ጉዞ እንዲረዳቸው እንደሆነ በግልፅ መታወቅ አለበት።

እንዳመጡትም በለመደው ወደ አሜሪካ ቢሮ ገባ ወጣ እያለ "መልከ ጥፉ በሥም ይደግፉ" የሆነውን አገር አድን(አገር አፍርስ) ንቅናቄ ከጥንት ኢሕአፓ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ በዘር በሽታ ከተለከፈው ጌታቸው በጋሻው ጋር አሥተባባሪ አደረጉት።አማራውም በአንድ ሰው ለምን ተወከለ ሲባሉ የተደራጀ ሥለጠፋና ሞረሽም በነሌንጮ ሥላልተደገፈ ሌላ ጊዜ ደግሞ የአማራ ድርጅት ሥለሌለ የሚል ማደነጋገሪያ ቀረበ።ቀጥሎም ሥለሌንጮ ባንዲራ ሲነሳ ዳዊት የሰጠው መልስ ሌሎቹም ረስተው ሥለመጡ ነው ብሎን አረፈው።ይች ናት አንድነት!!!

ዛሬ ደግሞ በጭፍን ከመከተል በሥተቀር፣ጠለቅ አድርጎ ማሰብ ለተሳነው ገንዘብ ከፋይና አጃቢ ሌላ ማደነጋገሪያ "መልከጥፉ በሥም ይደግፉ" የሆነ ብሔራዊ ንቅናቄ የሚል ተጀምሯል።

ሻለቃው! አሁን በቅርቡ ሌሎች ሲደራጁ መቀበልን፣አማራው ሲደራጅ መንጫጫትን ማውገዙን በሰማንበት ጆሯችን አማራ አሁንም እንዳልተደራጀ ፣ሌላም ሌላም በማለት ይቀጥልና "ኦሮሞ ከማዳጋስካር የመጣ ነው ብሎ ሞረሽ ፅፏል" የሚል አነጋገር ሠንዝሯል።ቀጥሎም ኦነግ ከመገንጠል ወደአለመገንጠል እንደመጣ ሊነግረን ሞክሯል።

ሻለቃው!ይህንን በማር የተጠቀለለ መርዝ ይዞ መቅረቡ ለእኔ አይደንቀኝም።ምክንያቱም በተደጋጋሚ እንደጠቀስኩት ከዚህ ቀደም የጠላት መሣሪያ በመሆን ዕድሜ ልኩን ሲሰራው የኖረውን የባንዳነት ተግባሩን እንደሚቀጥልበት ሥለማውቅ ነው።

ሻለቃው!አሁን በቅርብ ባደረገው ንግግር ላይ የተረዳሁት፣ሌላ የአማራ ድርጅት እነብርሀኑ ሊፈጥሩ ላይ ታች ሥለሚሉ፣ያን ሁኔታ ለማጠናከርና በአማራው ሥም የብአዴን ዓይነት ድርጅት ፈጥሮ ከተበከሉት ዘረኛ ድርጅቶች ጋር ለማዳበል ያደረው ንግግር እንጅ የአማራውን ለህልውናው መደራጀት አምኖበት አይደለም።ዛሬ የተናገረውን ነገ የማይደግም የተለመደ፣የሻለቃ ዳዊት ባንዳዊ አካሄድ እንደሆነ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር (**ኦነግ**) ከመገንጠል ወደአለመገንጠል እየተባለ ብዙ ጊዜ የሚለፈፈው **ሀሰት** ነው።ኦነግ አሁንም ኦነግ ነው።አቋሙም እስከዛሬዋ ዕለት ድረስ **መገንጠል** ነው።እነሌንጮ ካካበቱት የትግል ልምድ በመነሳት የተወሰኑት አሁንም እንደዱሮው በኦነግነት እንዲቀጥሉ አድርገው፣ የኦነግ መሥራቾች እነሌንጮ ለታ፣እነዲማ ነግዎ ደግሞ የውስጥ ትክክለኛ ገፅታቸውና አቋማቸው ያው እንደዱሮው ኦነግ ሆኖ ሳለ፣በአንድነት ሥም ሕዝብን ግራ አጋብቶ የሚመኙትን ለማግኘት የኦሮሞ ዴሞክራቲክ ግንባር (ኦዴግ) በማለት ታክቲክ ቀዬሩ።ለምሳሌ **የኦነግም ሆነ የኦዴግ** ድርጅቶች ሁለት ዓይነት ነን ቢሉም፣ባንዲራቸው ግን አንድ ነው አልተለወጠም። ይህ የታክቲክ ሥማቸው ወደህብረተሰቡ በመግባት ወያኔ ለራሱና ለእነሱ ያከፋፈለውን የዝሆን ድርሻ መሬቶች በክልል ሥም እንደያዙ የመቀጠሉን ሁኔታ ቋሚነት እንዲኖረው፣ኢትዮጵያኑ ህብረተሰብ አምኖ እንዲቀበልላቸው ለማስደረግ ነው። ሌንጮም ሆነ ሌሎቹ "ተቀይረናል" እያሉ የሚያደነቁሩንና ደጋግመው የሚነግሩን ፣ "አንድላይ ሆነን ተሥማምተንም ብንገባ የመገንጠሉ አንቀፅ 39 እና ክልልላችን አይቀዬርም" ብለው

ነው።ሌንጮ ባቲም በተደጋጋሚ የሚለው "አንቀፅ 39 እና ክልሉ ተሟልቶልናል፣ወያኔን የምንቃወመው በዴሞክራሲ ያቄ ነው" ብሎናል።አነብርሀኑም፣ሌሎቹም የዘር ድርጅቶች ይህንን ይጋራሉ።ሥለዚህ እውነተኞቹ የአንድነት ኃይሎችና አማራው የሚሉት ደግሞ የክልል ፌዴራሊዝምን አንቀበልም።ዛሬ ያሉት ክልሎች ፈርሰው የአሜሪካን መሰል ፌዴራሊዝም ወይም በዘር ያልተዋቀረ አስተዳደር ያሥፈልገናል ባዮች ናቸው።ሥለዚህ የኤትኒክ ፌደራሊዝም አቀንቃኝና የፀረ-ኤትኒክ አቀንቃኝ አንድ ሊሆን አይችልም።በአንድነት እንድንታገል ከተፈለገ ዙሪያ ጥምጥም እየሄድን ሕዝብን ግራ ማጋባቱን አቁመን፣ በቅድሚያ ኢትዮጵያንና ሠንደቃላማዋን ያላንዳች ቅድመ ሁኔታ መቀበል የግድ ነው።ከዚህ ውጭ የሚደረደሩ ምክንያቶች ፋይዳ የላቸውም።

መንታ ምላስ ይዞ መንታ መንገድ ላይ መቆም ይብቃ!

ዕውነትና ንጋት እያደር ይጠራል!

የከርሞ ሠው ይበለን!

ከበደ በለው